# የ"የትም ፍጪው ስልጣኑን ብቻ አምጪው" ተቃውሞ

በላይነህ ታምሩ

ትግራይ ኦንላይን April 24, 2014

የሀገራችን ተቃዋሚዎች አላዋቂነት ነገር አንገት የሚያስደፋ ከሆነ ዓመታት ተቆጥረዋል። አብዛኛዎቹ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅዶችን የሚያውቁ አይመስሉም፡፡ እንደ አጭር ርቀት ሩጫ ሁሉንም ነገር በፍጥነት ማጠናቀቅ የሚፈልጉ የተስፈኞች ስብስብ ናቸው፡፡ የአጭር ርቀት ሩጫቸው ግብ መዳረሻም፤ ያለ የምርጫ ሂደትና ያለ ህዝብ ይሁንታ በአቋራጭ ስልጣን እርካብን መቆናጠጥ ነው፡፡ በዚህም ከሀገራቸው ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ውሳኔ ይልቅ፤ ሌት ተቀን በውጭ ኃይሎች የሚሸከረከር ዴሞክራሲን እንደ ፍቅረኛቸው የሚናፍቁ ጉደኞች ናቸው፡፡

እነዚህ ወገኖች ለስሙ 'በህገ-መንግስታዊው ማዕቀፍ ውስጥ ሆነን ዓላማችንን በማራመድ ስልጣን እንይዛለን' ይበሉ እንጂ፤ በውስጣዊና በትክክለኛ አመለካከታቸው ግን እጣንና ከርቤ እያጨሱ 'የውጭ ኃይሎች ሆይ! በእናንተው መጀን ይዘናችኋል ለስልጣን ታበቁን ዘንድ እንለማመናለን፣ አሜን!' እያሉ የሚፀልዩ ናቸው፡፡ ከዚህ መለማመናቸው ባሻገር፤ ስልጣን ላይ የሚወጡበትን ጊዜ በውጭ ኃይሎቹ አማካኝነት ለማሳጠር፤ በቅጡ የማያውቁትንና በልካቸው ያልተሰፋውን የኒዮ-ሊበራሊዝም አስተሳሰብ ካባን ደርበው ይደሰኩራሉ፡፡

የውጭ ኃይሎች ለራሳቸው ፖለቲካዊ ፍላጎት ሲሉ በሚጠሯቸው ስብሰባዎች ላይ ሳይቀር እየተገኙ በሌለ ማንነታቸው "አሸሽ ገዳሜ፣ መቼ ነው ቅዳሜ?!" ማለት የሚቀናቸው አስገራሚዎች ናቸው። ኧረ እንዲያውም የውጭ ኃይሎች ከራሳቸው እሳቤ በመነሳት ስማቸውን ሲጠሯቸው አሁኑኑ አራት ኪሎ ቤተ-መንግስት የገቡ ያህል "እልል በቅምጤ" በማለት ራሳቸው በፈጠሩት ዓለም ውስጥ በቀቢፀ-ተስፋ በሃሳብ ዓለም እየዋኙ የሚንሳፈፉ ናቸው።

ታዲያ ይህ ተቃውሞአዊ ማንነት በመድብለ-ፓርቲ ስርዓቱ ውስጥ ዘለግ ላለ ጊዜ ያለ ምንም የነጠረ ፖሊሲና ስትራቴጂ ሲንጠራወዝ የቆየ ነው። የተቃውሞው ጎራ መሪዎች አንድ እግራቸውን ለይስሙላም ቢሆን ዴሞክራሲያዊነት ላይ አድርገው፣ ሌላኛውን ደግሞ የትክክለኛ ማንነታቸው መገለጫ በሆነው ኢ-ዴሞክራሲያዊነት ላይ በማድረግ እግራቸውን አንፈራጥጠው የተቀመጡ ናቸው። ይህ ማንነትም ካለፉት 22 ዓመታት ጀምሮ ዛሬ ላይ እስከደረሱት ነባር የፖለቲካ ተቃዋሚዎች ይሁኑም፣ ከተመሰረቱ ሁለት ዓመት እንኳን በቅጡ ያልሞላቸው የተቃውሞ አታሞ ደላቂዎች ያው ነው—"የማን ዘር ጎመን ዘር" እንዲል የሀገራችን አርሶ አደር።

እርግጥ ለዚህ አባባሌ ረጅም ርቀት ሄጄ ላደክማችሁ አልፈልግም። በቅርቡ በምርጫ ቦርድ ባህር መዝገብ ውስጥ ከተመዘገበ አንድ ዓመት ከመንፈቅ ብቻ የስቆጠረው፣ ሰላማዊ ሰልፍ ጠርቶ በሃይማኖት ሽፋን የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፅንፈኛ "ሲራራ ነጋዴዎችን" አጀንዳ ያራመደው ብሎም የኒዮ-ሊበራል ሃይሎች የቀለም አብዮት ተላላኪ የሆኑት የሰማያዊ ፓርቲ ፕሬዚዳንት ኢንጂነር ይልቃል ጌትነት በተለያዩ ጊዜያት የደሰኮሯቸውን ጉዳዮች ማንሳት ይቻላል። ኢንጂነር ይልቃል በአንድ ወቅት 'አዲስ አበባ በሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ ውስጥ ተጠርቼ የ35 የውጭ ሊጋሽ ሀገራት አምባሳደሮች በተገኙበት ኢትዮጵያንና ቀጣናውን የተመለከተ የዳሰሳ ፅሑፍ አቀረብኩ' ያሉትንና፣ በቅርቡ ደግሞ 'ዋሽንግተን ሄጄ ልሸለም ስል የኢትዮጵያ መንግስት ከለከለኝ' በማለት የዘበዘቡት ድርሰት ይህን ዕውነታ የሚያመላክት ነው።

ለነገሩ ኢንጂነሩ አሜሪካ ኤምባሲ ተጠርተው ያሻቸውን መናገራቸው፤ በሀገራችን ውስጥ ስር በመስደድ ላይ ያለው የዴሞክራሲያዊ ባህል ግንባታ ስርዓት መገለጫ እንጂ ሰውዬው ድንቅና ብርቅ አድርገው

እንደተናገሩት አይደለም። ምክንያቱም በአንድ ሀገር ውስጥ ያለ ኤምባሲ መደበኛ ስራው በሀገሩና ተቀማጭ በሆነበት ሀገር እንደ ድልድይ ሆኖ በማገልገል በሁለቱ ሀገሮች መካካል ያለውን ግንኙነት ይበልጥ ማጠናከር እንጂ በሀገራት የውስጥ ጉዳይ ገብቶ የመፈትፈት መብት ስለሌለው ነው። እናም በእኔ እምነት ኢንጂነሩ አቀረብኩት ያሉት ጉዳይ ምንም ይሁን ምን ለኤምባሲውም እንኳን ቢሆን ከጠቅላላ ዕውቀት የዘለለ ሊሆን አይችልም። ለዚያውም በእኔ እምነት አማተር ፖለቲከኛ መሆናቸውን ራሳቸው በተለያዩ ጊዜያት የመሰከሩት ኢንጂነሩ የሀገራችንንም ይሁን የቀጣናውን ሁኔታ የመናገር አቅምና ዕውቀት የላቸውም።

ያም ሆነ ይህ ግን በዚህ ፅሑፍ አቅራቢ እምነት የሰማያዊ ፓርቲ ፕሬዚዳንት አሜሪካ ኤምባሲ ውስጥ ተሰብስበው፤ "የፓርቲዬን ዝርዝር የፖሊሲ አማራጮች ለማሳየት ሞክሬያለሁ፣ አምባሳደሮቹ ኢትዮጵያ ውስጥ የአረቡ ዓለም አብዮት ይመጣል ወይ? የሚሉና ሌሎች ተመሳሳይ ጥያቄዎችን ጠይቀውኛል፣ የ2007 ምርጫን በተመለከተም ፓርቲዬ እንደሚያሸንፍ ገልጫለሁ እንዲሁም በኢትዮጵያ ጋዜጠኞች የመንግስትን አሰራር በመተቸታቸው፣ በፖለቲካ አመለካከታቸውና መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይግባ በማለታቸው መታሰራቸውን በማስረዳት የለጋሽ ሀገር አምባሳደሮች ሁኔታውን እንዲያስተካክሉ ግፊት አድርጌያለሁ" ሲሉ የተናገሩት አባባል የሚደንቅ ብቻ ሳይሆን፣ የሰውዬውን የፖለቲካ ተክለ-ሰውነት በአሳፋሪ ሁኔታ ግምት ውስጥ የከተተ ነው። ዕውቀት አጠርነታቸውንም አፍ አውጥቶ የተናገረ። ለምን? ቢሉ፤አባባላቸው በሌለ ማንነትና ነባራዊ ሁኔታ የተነገረ፣ ከፍ ሲልም በነብይነት የተተነበየ እንዲሁም ፓርቲያቸው ሰላማዊ ሰልፍ ጠርቶ በፍርድ ቤት የተያዘ የሃይማኖት አክራሪዎችንና የተጠርጣሪ አሸባሪዎችን አጀንዳ የራሱ አስርጎ እንዳራገበው ሁሉ፤ አሁንም ይህንኑ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አካሄዱን በመድገሙ ነው። እናም በእኔ እምነት ኢንጂነሩና ፓርቲያቸው እነዚህን ጉዳዮች ለማውጋት ያልደረሱ ብቻ ሳይሆኑ፣ እንደ ጀማሪ ፖለቲከኛ በዴሞክራሲ ብረት ድስት ውስጥ በደንብ ተቀቅለው መብሰል ያለባቸው ይመስለኛል—ገና ለአቅመ-ተቃዋሚነት ለመድረስ ዳዴ እንኳን እያሉ አይደለምና።

ያም ሆነ ይህ ግን ሰውዬው "ተናገርኩ ወይም አስረዳሁ" ያሏቸውን የ"ላም አለኝ በሰማይ..." የተቃውሞ ቅዠቶችን በፈርጅ በፈርጁ መመልከት ፓርቲው ከሚከተለው እጅግ አናሳ ህዝብ በተጨማሪ የውጭ አምባሳደሮችን በሌለ ስብዕናው እንዴት ለማታለል እንደሞከረ ለመረዳት አያዳግትም። እስቲ በመጀመሪያ ደረጃ ጨቅላው ሰማያዊ ፓርቲ ምን ዓይነት አማራጭ ፖሊሲ እንዳለው እንመልከት። ዕውን የኢንጂነሩ ፓርቲ አማራጭ ፖሊሲ ይኖረው ይሆን እንዴ?...

እርግጥ እዚህ ላይ ኢንጂነር ይልቃል አማራጭ ፖሊሲ ያሉትን ነገር ምን እንደሆነ በቅድሚያ መረዳት ያስፈልጋል። ለመሆኑ 'አማራጭ ፖሊሲ' ምን ማለት ነው?...'አማራጭ ፖሊሲ' ማለት ከገዥው ፓርቲ የተለየ የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ መስመርን በተዘረዘረ መንገድ ማቅረብ ነው። ከዚህ አኳያ የሀገራችን ተቃዋሚዎች በገዥው ፓርቲ አሰራሮች ላይ ተንተርሰው ጭፍን የጥላቻ ዲስኩር ከማሰማት እንዲሁም የማያውቁትን የኒዮ-ሊበራሊዝም ቃርሚያዎችን በጥራዝ ነጠቅነት ከማቀንቀን በስተቀር ይህ ነው የሚባል ፖሊሲም ይሁን ስትራቴጂ የላቸውም፤ ኖሯቸውም አያውቅም።

ዋነኛ ፖሊሲያቸውና ስትራቴጂያቸው በሀገር ውስጥ በተለያዩ ነባራዊ ሁኔታዎች አማካኝነት የሚፈጠሩ ችግሮችን በማነፍነፍ ብሶትን ማራገብ ብሎም በአጀንዳነት ይዞ ማቀንቀን ነው። ለነገሩ እንኳንስ ገና ጅምር ላይ ያለ የፖለቲካ ፓርቲ ቀርቶ ዕድሜ ጠገቦቹ የሀገራችን ተቃዋሚ ፓርቲዎች በግልፅ የተዘረዘረ ፖሊሲ የላቸውም። እናም ኢንጂነሩ አማራጭ ፖሊሲ ያሉት ነገር የገዥውን ፓርቲ ተግባራት እየተከታተሉ ማጠልሸት እንጂ የራሳቸው ወጥ የሆነ የፖለቲካ አቅጣጫን አይደለም። ለዚህ ደግሞ ፓርቲያቸው በተቋቋመ ጥቂት ጊዜ ውስጥ ይዘውት የተነሱት አጀንዳ ይኸው በሌሎች ስራ ላይ ተንጠላጥሎ ዲስኩር ማሰማት መሆኑን በየጊዜው ከሚያራምዱት አጓጉል ትንታኔ ለመረዳት ይቻላል። ምክንያቱም ፓርቲው ዓላማውን ለህዝብ ከማስረዳት ይልቅ በተለያዩ ወቅቶች የመንግስትን ስራዎች በማጥላላት ላይ መሰለፉ እንዲሁም በህግ የተያዙ ጉዳዮችን ለመቀልበስ ማሰቡ ብሎም ከህገ-መንግስቱ ጋር በመላተም በአክራሪነት

የተጠረጠሩ ግለሰቦች ጋሻ ጃግሬ መሆኑ የዚህ ዕውነታ ሁነኛ አስረጅ በመሆኑ ነው። እናም በእኔ እምነት የኢንጂነር ይልቃል ፓርቲ እንኳንስ አማራጭ ፖሊሲ ሊኖረው ቀርቶ ስለ አማራጭ ፖሊሲ ሰምቶም የሚያውቅ አይመስለኝም።

የዚህን ፅሑፍ አቅራቢ እጅግ ያስገረመኝ ሌላው ጉዳይ ኢንጂነሩ "...አምባሳደሮቹ ኢትዮጵያ ውስጥ የአረቡ ዓለም አብዮት ይመጣል ወይ?" በማለት የተናገሩት "ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ" ዓይነት ቀቢፀ-ተስፋ ነው። እርግጥ ይህ አባባል ሰውዬውና ፓርቲያቸው ስልጣንን ያለ ህዝብ ይሁንታ  በአቋራጭ በአመፅ ለመያዝ ያለመ ነው። ግና ይህ ዓይነቱ የቀን ቅዥት በአዲስቷ ኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ የማይሰራ መሆኑን ሰውዬው ማወቅ ያለባቸው ይመስለኛል—ምክንያቱም ኢንጂነሩ የዓረቡ ዓለም አብዮት እንዴት እንደተነሳ እንዲሁም የሀገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ጭርስኑ ስለማያውቁት ነው። ምንም እንኳን የሰውዬው የአመፅ ፍላጐት ዲስኩር "አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል" እንዲሉት ዓይነት ቢሆንም፤ የዓረቡ ዓለም አብዮት እንዴት እንደተነሳ ማስታወስ ተገቢ ይመስለኛል።

እንደሚታወቀው የአረቡ ዓለም ማህበራዊ አብዮት የተቀጣጠለበት ምህዳር ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር ለየቅል ነው። አብዛኛው የዓረብ ዓለም ዴሞክራሲን የማያውቅ፣ በንጉስ ወይም በአሚር የሚተዳደር፣ የቤተሰባዊ መተካካት እንጂ ምርጫን አካሂዶ የማያውቅ፣ ከነዳጅ የሚገኘው ገቢ የጥቂቶችን የገንዘብ አቁማዳ ብቻ የሚሞላ እና እጅግ የሚበዛው ህዝብ ተጠቃሚነቱ "አድሮ ቃሪያ" የሚሉት ዓይነት መሆኑ ለማህበራዊ አብዮቱ መነሻነት የሚጠቀሱ ጥቂት አብነቶች ናቸው። በተለይም መንግስታቱ በየጊዜው እየጨመረ የመጣውን የኑሮ ውድነት መቋቋም የተሳናቸውና ወጣቶቻቸውን በስራ ፈጠራ በየደረጃው ተጠቃሚ ማድረግ ያልቻሉ በመሆናቸው የአብዮቱ ሰለባ ሊሆኑ ችለዋል።

እኛ ሀገር ውስጥ ያለው ሁኔታ ግን ከዚህ በፍፁም የተለየ ነው። ዴሞክራሲያዊ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ላለፉት 23 ዓመታት በሂደት እየተገነባ ዛሬ ላይ መድረስ ችለናል። ስልጣን የመብቱ ባለቤት በሆነው ህዝብ አማካኝነት በምርጫ የሚገኝ መሆኑም ባለፉት አራት የምርጫ ሂደቶች ታይተዋል። አምስተኛውም በቀጣዮ ዓመት ይካሄዳል። ሀገሪቱን እየመራ የሚገኘው ገዥ ፓርቲ ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት በአማካይ ከአስር በመቶ በላይ ዕድገት በማስመዝገብ ህዝቡን በየደረጃው ተጠቃሚ ማድረግ ችሏል። በተለይም ወጣቶችንና ሴቶችን በአነስተኛና ጥቃቅን የስራ መስኮች በማደራጀት ከሀገሪቱ ልማታዊ ዕድገት ተጠቃሚ እንዲሆኑ አድርጓል። በመሆኑም እነ ኢንጂነር ይልቃል የሚመኙት የአረቡ ዓለም አብዮት ኢትዮጵያ ውስጥ መቼም ቢሆን ሊመጣ አይችልም—የሰማያዊ ፓርቲና የላኪዎቹ የቀን ቅዠት ካልሆነ በስተቀር።

ሁላችንም እንደምናውቀው የሀገራችን ህዝብ በመንግሥት ትክክለኛ የልማት አቅጣጫዎችና ፖሊሲዎች ተመርቶ ተጠቃሚነቱን ከጊዜ ወደ ጊዜ ከማረጋገጡ ባሻገር በተነደፈው የአምስት ዓመት ዕቅድ "የነገ ሰው" እንደሚሆን ባለሙሉ ተስፋ ነው፡፡ ለዚህም ነው ቁርስና ምሳን ትቶ ለታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ እውን መሆን ቦንድ በመግዛት ከዳር እስከ ዳር የተነቃነቀው፡፡ ማንኛውም የዚህ ፅሁፍ አንባቢ እንደሚገነዘበው፤ ይህ ለሀገሩ ቀናዒ የሆነና አመዛዛኝ ህዝብ ለአመፅ አላሚዎች ሲል የአክራሪ ኒዮ-ሊበራል ኃይሎች የሀገር ውሰጥ ጉዳይ ፈፃሚዎች "የኮሚሽን" አሉባልታዎችን ሊሰማ አይችልም። ህዝቡ ላለፉት 23 ዓመታት የተጎናፀፈው የሰላም እፎይታ ፀዳል በሰማያዊ ፓርቲ ዓይነት የቀለም አብዮተኞች ተላላኪ ምናባዊ ቅዥት እንዲደፈርስበትም አይሻም፡፡ በልዩነት ላይ ባለ አንድነት ተከባብሮ የመሰረተው ዴሞክራሲያዊ ስርዓትም፤ በሌላው ዓለም የተከናወነ ነገር እኛ ሀገርም ካልተፈፀመ በሚሉ የቀለም አብዮት ተላላኪዎች የኋሊት እንዲቀለበስበት አይፈልግም። ታዲያ እነዚህን ሁሉ ትሩፋቶች እያጣጣመ ያለ ህዝብ፤ ከእርሱ ጋር የማይተዋወቀውን አረባዊ አብዮት የሚያስብበት ምንም ምክንያት የለውም፡፡ እናም የአረቡ ዓለም አብዮት ቀቢፀ-ተስፋ ሊኖር የሚችለው በኢንጂነር ይልቃል አመፅ ናፋቂ ጭንቅላት ውስጥ ብቻ  መሆኑን ፓርቲያቸውና ሰውዬው መረዳት ያለባቸው ይመስለኛል፡፡

እናም ሰማያዊ ፓርቲ የተሰኘው የቀለም አብዮት አመፃ ናፋቂ ቡድን ይህን የሀገራችንን ነባራዊ ሁኔታ ሳይረዳ በደመ ነፍስ በራሱ የሃሳብ ማዕበል ውስጥ ሰጥሞ ዲስኩር ማሰማቱ፤ ስለ ሀገራችንና ስለ ህዝቧ ያለው የአስተሳሰብ መለኪያ በራሱ አላዋቂ ህሊና ውስጥ ብቻ የታጠረ መሆኑን ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡ በጭፍን ጥላቻ በመመራት እንዲሁም የላኪዎቹን አጀንዳ ምን እንደሆነ እንኳን በቅጡ ሳይገነዘብ ስለ አዲሲቷና በፈጣን የዕድገት ባቡር ላይ ስለ ተሳፈረችው ኢትዮጵያ ለማውራት መሞከሩም አሳፋሪ ነው፡፡ ፓርቲው ዛሬን በማያውቀው ትናንት ዓይን የሚለካ እንዲሁም ህዝቡን ሳይሆን አክራሪ ኒዮ-ሊበራሎችን ተማምኖ የሞኝ ለቅሶን በማላዘን የቀለም አብዮትን የሚናፍቅ ነው፡፡ ዳሩ ግን ህዝቡ ከተሳፈረበት የልማት ባቡር ላይ ወርዶ፤ የላኪዎቹን የቀለም አብዮት የሸንፈት ቁስልን የሚያክምበትና እንደ ማንኛውም ተቃዋሚ በአብሾ መልክ በየጊዜው የሚነሳበትን የአመፅ ዛር የሚያስተናግድበት ቅንጣት ያህል ፍላጎት የሌለው መሆኑን ማወቅ ያለበት ይመስለኛል፡፡ ለምን ቢሉ በሌለ ነባራዊ ሁኔታ የሚያልመው የአረባብ አብዮት ቅዥታዊ ህልሙ ጉም የመዝገን ያህል በመሆኑ ነው፡፡

የሀገራችን የተቃውሞ ጎራ ምንም ዓይነት ፖለቲካዊ ዓላማና ግብ ሳይኖረው በ“የትም ፍጪው ስልጣኑን አምጪው” መርህ የሚመራ መሆኑን ያረጋገጠው ሌላኛው ጉዳይ፤ ተላላኪው ኢንጂነር ይልቃል ያለ አንዳች ሃፍረት የህዝብን ሉዓላዊ መብት በመደፍጠጥ በ2007 ምርጫ እንደሚያሸንፉ በጥንቆላ መልክ መተንበያቸው ነው። እርግጥ ምኞት አይከለከልም። ማንም ያሻውን ሊለፍፍ ይችላል። ኢንጂነሩም እንኳንስ በ2007 ምርጫ እንደሚያሸንፉ እርግጠኛ መሆን ቀርቶ ‘በቀጣዩ ዓመት ባን ኪ ሙንን በመተካት የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ እሆናለሁ’ ቢሉም መብታቸው ነው። ከልካይ የላቸውም። ግን…ግን ምኞት ገደብ ያለውና በትክክለኛ ማንነት ላይ የተመሰረተ መሆን ይኖርበታል። ያለ አቅምና በሌለ ማንነት የማይሆኑትን ነገር ማለምና መመኘት፤ “እንቁራሪት በሬን አክላለሁ ብላ ፈንድታ ሞተች” የተባለው ተረት መገለጫ መሆንን ብቻ ነው— የሚያስገኘው ትርፍ።

ከዚህ አንፃር ከተመሰረተ ዓመት ከመንፈቅን ብቻ ያስቆጠረው የኢንጂነሩ ፓርቲ ገና ጮርቃ ነው። የፖለቲካ ‘ህሁ’ ቆጣሪ። ሌላው ቀርቶ በህዝቡ ዘንድ እንኳን እምብዛም የሚታወቅ አይደለም። በደፈናው ከመቃወም በስተቀር ዓላማና ግብ የለውም። እናም የማይታወቅና የነጠረ የፖለቲካ መስመር የሌለው ፓርቲ ገና ምርጫው የዓመት ዕድሜ ያህል እየቀረው ‘አሸንፋለሁ’ ማለቱ ለማንም ግልፅ አይደለም። ሆኖም ይህ አባባሉ አንድ ነገር እንድንጠረጥር ያደርገናል። እርሱም ፓርቲው በአክራሪ ኒዮ-ሊበራሎች አይዞህ ባይነት ምርጫው ከመከናወኑ በፊት አሊያም ከተከናወነ በኋላ የቀለም አብዮት በማካሄድ የህዝቡን ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤትነት ለመቀማት ዝግጁ መሆኑን ነው። ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነቱ የተላላኪነት ተግባር በምርጫ 97ትም ይሁን በምርጫ 2002 ወቅት ተሞክሮ ያልሰራ በመሆኑ ሊሳካለት አይችልም። ለምን ቢባል ሀገራችን ውስጥ የቀለም አብዮትን ማካሄድ የሚቻልበት ነባራዊ ምህዳር የሌለ በመሆኑ ነው።

የሀገራችን ዴሞክራሲያዊ የመድብለ-ፓርቲ ስርዓት ለእንዲህ ዓይነቱ ፀረ-ህዝብ ተግባር ትናንትም ይሁን ዛሬ የተወው፣ ወደፊትም የሚተወው አንዳችም ዓይነት ቀዳዳ የለም። እናም ፓርቲው ምናልባትም በሌሎች ሀገር ውስጥ ጣልቃ የሚገቡበት ቀዳዳ ሲጠፋቸው አንዳንድ የስልጣን ጥም እንጂ ሀገራዊ ፍቅር የሌላቸው ባንዳ ተቃዋሚዎችን እየመለመሉ የቀለም አብዮት በማካሄድ የህዝቦችን ስልጣን በሁከት ለማስቀማት ባሰፈሰፉ ፅንፈኛ ኒዮ-ሊበራሎች ታግዞ ለዚህ ተግባር መታጨቱን እንቅስቃሴው ስለሚያስታውቅ ከወዲሁ ራሱን መፈተሽ ያለበት ይመስለኛል።

በውጭ ሃይሎች በሚቀመር ደም አፋሳሽ የቀለም አብዮት የሚገኝ በአቋራጭ ስልጣን የማግኘት ህልም ኢትዮጵያ ውስጥ በሩ የተከረቸመበት ብቻ ሳይሆን ከቶም ገቢራዊ ሊሆን የሚችል አይደለም። እንዲያውም ፓርቲውን በፀረ-ህገ-መንግስታዊነት በማስፈረጅ ሊያስጠይቀው የሚችል አሳፋሪ ተግባር ነው። በመሆኑም እንደ ዜጋ ኢንጂነሩንና ፓርቲያቸውን “ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ…” የሚለውን ሀገራዊ ይትብሃል ባስታውሳቸው ከፅድቅ እንጂ ከኩነኔ የሚያስቆጥርብኝ አይመስለኝም። ሰማያዊ ፓርቲን እንደ ሀገር በቀል

ሰላማዊ ፓርቲ እንጂ በውጭ ሃይሎች ተመርቶ ሀገር ውስጥ መርዝ ይዞ እንዲበቅል የተደረገ ተላላኪ የፖለቲካ ድርጅት ሆኖ ማየት ዘግናኝ ነውና።

ሌላኛው ኢንጂነሩ ያሰሙት ዲስኩር "ጋዜጠኞች የመንግስትን አሰራር በመተቸታቸው፣ በፖለቲካ አመለካከታቸውና መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይግባ ስላሉ መታሰራቸውን አስረድቻለሁ" የሚል ነው። ይህ ከዕውነት የራቀንን ጉዳይ የማቀንቀን ብሎም በህግ የተያዘ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ ገብቶ የመፈትፈት አካሄድ ፈፅሞ ተቀባይነት የሌለው ነው። እነደሚታወቀው ሀገራችን ውስጥ በፃፈው ፅሑፍ ምክንያት በህግ ጥላ ስር የዋለ አንድም ጋዜጠኛ የለም።

በህግ ጥላ ስር የሚገኙት ግለሰቦች በወንጀለኛነት ተግባር ተሰልፈው የተረጋገጠባቸው አሊያም የድርጊቱ ተጠርጣሪዎች ብቻ ናቸው። ያም ሆነ ይህ ግን እንደ የትኛውም ሀገር ሁሉ፤ መንግስት የሀገሪቱን ህግና ስርዓት የመጠበቅም ሆነ የማስጠበቅ መብትና ግዴታ አለበት፡፡ በመሆኑም ማንኛውንም ፀረ -መንግስትና ፀረ-ህዝብ ኃይልን የመመከትና ዜጎቹን የመጠበቅ ተግባር በእርሱ ጫንቃ ላይ የወደቀ ነው፡፡ በመሆኑም ህግና ስርዓትን የተላለፉት ግለሰቦች ጋዜጠኞችም ይሁኑ መሃንዲሶች አሊያም ባለስልጣናትም ይሁኑ ፖለቲኞች ወይም ተኳሾችም ይሁኑ ቀዳሾች…ወዘተ. ማንኛውም ዜጋ የሚያከናውኑትን ህገ-ወጥ እንቅስቃሴዎች ማምከንና ወንጀለኞችን የህግ ተጠያቂ ማድረግ ይኖርበታል። እናም አንድ ግለሰብ ጋዜጠኛ ስለሆነ ብቻ ወንጀል ሲሰራ የሚታለፍበት አሰራር የሌለ መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው—ወንጀለኛ ያው ወንጀለኛ ነውና። እናም ከዚህ አኳያ የኢንጂነሩ አሉባልታ ተቀባይነት የሌለው ብቻ ሳይሆን የህግ የበላይነትን ተቃርኖ የተነገረ ሐሰት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ጉዳይ ነው ባይ ነኝ።

ሁሌም ቢሆን ሃይማኖትንና ፅንፈኞችን መደገፍ እንደ አንድ የፖለቲካ ስልት የሚከተለው ሰማያዊ ፓርቲ፤ መንግስት በሃይማኖት ውስጥ ጣልቃ እንደሚገባ አስመስሎ በማውራት የሌለን ተጨባጭ ሁኔታ ለመፍጠር ጥረት ያደርጋል። ሰውዬው 'አሜሪካ ኤምባሲ ውስጥ ነገርኳቸው' ላሏቸው አምባሳደሮችም የቀጠፉት ይህንኑ ጉዳይ ነው—በጋዜጠኞች አመካኝቶ። እርግጥ ፓርቲው ሁከትን ከሚሹ ሃይማኖታዊ ፖለቲከኞች ጋር ተለጥፎ የሚያቀነቅነው የሌለ ፀረ-ህገ-መንግስታዊ ወሬ ሰላምን የማደፍረስ የቀለም አብዮቱ መንገድ አንድ ማሳያ ሊሆን ይችላል። ይሁንና ይህ ተስፋው በአብዛኛው ሙስሊም ዘንድ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን እየጎመዘዘውም ቢሆን ሃቁን ሊጎነጨው ይገባል። ለምን ካለም፤ ነገሩ ወዲህ ነው።….

እንደሚታወቀው የሀገራችን ሙስሊም እርስ በርሱ ብሎም ከሌሎች የሃይማኖት ተከታዮች ጋር ያለው ታሪካዊ ግንኙነት በመከባበርና በወንድማማችነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህ ለዘመናት ይዞት የመጣው ባህሉ በጥቂት አክራሪዎች ሊበረዝ የሚችል አይደለም፡፡ በሰላም ተዋዶና ተፋቅሮ የመኖር ዘይቤን የሚከተለው የሙስሊሙ ምዕመን ሰማያዊ ፓርቲ እንደሚመኘው ሳይሆን፣ እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የሰላምን ጥቅም አሳምሮ የሚያውቅ ነው፡፡ በሀገሪቱ ውስጥ ሰላም ቢደፈርስ ተጎጂ እንጂ ተጠቃሚ እንደማይሆን ስለሚገነዘብም፤ ለጥቂት ፀረ-ሰላም ኃይሎች ቦታ የሚሰጥበት ምንም ዓይነት ምክንያት ሊኖረው አይችልም፡፡ እናም ሰላምን በመውደዱ እፍኝ በማይሞሉ አክራሪዎችና እንደ ኢንጂነሩ የሁከት ሴራ አምላኪነት ፓርቲ ዓይነት የራሳቸውን ፖቲካዊ አጀንዳ አንግበው የሚንቀሳቀሱ ፀረ - ህገ -መንግስት ኃይሎች አመፃን ሊሰማው አይፈልግም፡፡

ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ሙስሊሙ ማህበረሰብ መንግስት በህገ- መንግስቱ ላይ የተደነገገውን "የሃይማኖትና የመንግስት መለያየትን" መርህ ተከትሎ፤ ትክክለኛ ጥያቄዎችን ይዞ ይንቀሳቀስ በነበረው ምዕመን ውስጥ እንደ እባብ ተሰግስገው መርዛቸውን ሲረጩ የነበሩ እጅግ አነስተኛ ፀረ - ሰላም ኃይሎችን በመከላከል የህግ የበላይነት ስራን እያከናወነ መሆኑንም ተረድቷል፡፡ እነ ሰማያዊ ፓርቲ የሚደግፉት አክራሪነት የሰብዓዊ መብት አንኳ የሆነውን የእምነት ነጻነት በመስበር፣ ሰዎችን 'የእኔን እምነት ብቻ ተከተል' በሚል አስገዳጅ ድንጋጌ ማንነትን የሚነጥቅ ፀረ- ዴሞክራሲያዊ እሳቤ እንደሆነም አሳምሮ ያውቃል፡፡ አብዛኛው

ምዕመን ትናንት እርሱ ያልጠራው ስብሰባ ሲካሄድ፣ ከውጭ ሀገር ድረስ በመምጣት የሁከት መቀስቀሻ ወረቀት ለመበተን ሲሞክር ብሎም በአምልኮት ሥነ - ሥርዓቱ ወቅት ከሃይማኖት አባቶች ድምጽ ማጉያ እየተነጠቀ የነውጥ ጥሪ ቅስቀሳ ...ወዘተ እየተካሄደ መሆኑን ሲመለከት፤ መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ ሳይገባ ህግና ስርዓትን በማስከበር ግዴታው ላይ መሰማራቱን በእርግጠኝነት አውቋል፡፡

እናም ጥቂት የኢንጂነሩ ዓይነት ፖለቲከኞች እንዲሁም ሃይማኖታዊ አክራሪዎች የራሱን ፍትሃዊ ጥያቄዎች በራሳቸው የነውጥ መንገድ ሊዘውሩትና ወደ ማይፈልገው አቅጣጫ ሊመሩት እንዳቆበቆቡ ዛሬ ላይ ሆኖ በመረዳቱ፤ የአመፃ በርን ክርችም አድርጎ ዘግቷል፡፡ በዚህ ሰላም ወዳድ ባህሪውም በውስጡ ተሰግስገው የነበሩ ጥቂት ነውጠኞች ከአብዛኛው ህዝበ - ሙስሊም መሃል ተናጥበው እንዲወጡ አድርጓቸዋል— ልክ እብቁን ከጥሬው የመለየት ያህል አንጓሎ በማሳየት፡፡ እናም ይህ ተግባሩ ለህልም ፍጀታ ካልሆነ በስተቀር ለሰማያዊ ፓርቲ ፍላጎት ምቹ አይደለም። ለዚህም ነው ፓርቲው የሚያስበው የሁከት ፍላጎት የማይሳካ መሆኑን አስረግጬ የምከራከረው። ምክንያቱም አብረውት ያሉት ልክ እንደ እርሱ የመንግስትና የሃይማኖትን የመለያያ ገመድ በመበጣጠስ ለአሸባሪነት ያቀበቆቡ ጥቂት አክራሪዎች እንጂ ሰላም ወዳዱ አብዛኛው የሙስሊም ምዕመን ባለመሆኑ ነው።

ሌላኛው የኢንጂነሩ ዲስኩር የሚያጠነጥነው ደግሞ ‘ዋሽንግተን ሄጄ ልሸለም ስል የኢትዮጵያ መንግስት ከለከለኝ’ የሚለው አስቂኝ ጉዳይ ነው። እኔ እስከሚገባኝ ድረስ የስልጣን ሸላሚና ሻሪ የሆነውን የሀገራችንን ህዝብ ነው። ያም ሆነ ይህ ግን የሰውዬውን አስቂኝ ተረት ይበልጥ በውሸት የታጀለ መሆኑን የሚያረጋግጠው በቅርቡ አዲስ አድማስ ጋዜጣ ከአሜሪካ ኤምባሲ በኩል የተገኙ መረጃዎችን ጠቅሶ እንዳስነበበው፤ ኢንጂነሩ ተመረጥኩ የሚሉበት ነገር የአሜሪካ ስቴት ዲፓርትመንት በየዓመቱ ለሚያዘጋጀው የሊደርሺፕ ፕሮግራም እንጂ ሽልማት አለመሆኑን ነው። እናስ ትክክለኛው ማን ይሆን?— ተላላኪው ወይስ የኤምባሲው ሰዎች?...

ለነገሩ ማናችሁ ትክክል እንደሆኑ የዚህን ፅሑፍ አቅራቢ የሚያገባው ጉዳይ ባይሆንም፤ አንድ ዕውነታ ግን ፊት ለፊታችን በእርግጠኝነት ቆሞ ይታያል። እርሱም የትኛውም የሀገር ውስጥ የሚገኝ የፖለቲካ ፓርቲ ሽልማትን የሚያገኘው ከራሱ ህዝብ እንጂ ከውጭ ሃይሎች አለመሆኑን ነው። እኔ እስከማውቀው ድረስ ለህዝቦች የዘመናት ጥያቄ የተዋደቁት ታጋዮች (ምንም እንኳን ሰውዬው በፖለቲካ ስም የሚነግዱ የቀለም አብዮተኛ እንጂ ታጋይ ባይሆኑም) ህዝባዊ ሽልማት ያገኙት ደደቢትና አሲንባ ሄደው እንጂ፤ የዋሽንግተንን ደጅ በመጥናት አይደለም። ከአዲስ አበባ ዋሽንግተንና ብራስልስ በአውሮፕላን ተመላልሰው አይደለም— የደደቢትንንና አሲንባን በእግራቸው አቆራርጠው እንጂ። እንደ እውነቱ ከሆነ ሸላሚዎቹ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች እንጂ ከቶም ቢሆን የውጭ ሃይሎች አይደሉም። ግና ሰውዬውና ፓርቲያቸው በሀገራችን ህዝቦች ላይ የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል እምነት ስለሌላቸው እንዲሁም በፖለቲካው ስም በኪራይ ሰብሳቢነት የተሰለፉ በመሆናችሁ የሀገራችንን ህዝብ የስልጣን ባለቤትነትን ከመጤፍ ባለመቁጠር ኮሮጆአችሁን አንከርፍፈው ምንትስ እንዳየ አሞራ የውጭ ሃይሎች ዘንድ ማንዣበባቸው ማንንም አይደንቅም።ምክንያቱም የ“የትም ፍጪው ስልጣኑን ብቻ አምጪው” የተቃውሞ ፖለቲካ ዋነኛ መገለጫው ህዝብን መናቅ ስለሆነ ነው።